# እንዲኖረን የምንፈልገው መንግሥት?

በአገራችን ረጅም ታሪክ ውስጥ ብዙ መሪዎች ተነስተው ነግሰውና ስርዓት መስርተው አልፈዋል።እነዚህ በተለያየ ጊዜ በሃይል ስልጣን ይዘው፣ዘውድ የጫኑ መሪዎች በአገራችን የአስተዳደር ታሪክ ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ ይዘዋል።በመሰላቸውና በፈለጉት መንገድ ለማስተዳደርና ለመምራት ጊዜው፣አቅሙና ችሎታቸው በሚፈቅድላቸው መሰረት በጎና መልካም ፣መጥፎና አስከፊ ሥራ ሠርተው አልፈዋል።የሌሎችም አገሮች ነገሥታቶች ከዕኛዎቹ ነገሥታቶች የተለየ የሥልጣን አያያዝና የአስተዳደር ስልት አልተጠቀሙም።በፈላጭ ቆራጭነት ከሁሉም በላይ የሆነ ሥልጣን ነበራቸው።የሕዝቡም የአገሩም ባለቤቶች ነበሩ።ሃይላቸው ሲዳብር ሲፈቅድ በአስተዳደራቸው ውስጥ ለማካተት የከባቢያቸውን መሬትና ሕዝብ በውድም በግድም እንዲቀበላቸው፣በመንግሥታቸው አስተዳደር ሥር እንዲሆን አድርገዋል።አሁን በዓለም ላይ ድንበራቸው ሰፍቶና ተከብሮ፣ ገነው ለመታየት የበቁት አገሮች ቀደም ሲል የነበሩት መሪዎቻቸው ባደረጉት ትግልና ዘመቻ በጣሉት አገራዊ መሠረት ላይ ተከታዩ ትውልድ ጠብቆ ከጊዜውና ከትውልዱ ጋር የሚጣጣም ስርዓት አስፍኖ በመቀጠሉ ነው።

እኛም ኢትዮጵያውያን የሌላው አገር ሕዝብ ያለፈበትን የታሪክ ጎዳና ከሞላ ጎደል ተከትለን አሁን ካለንበት ደረጃና የታሪክ ወቅት ላይ ደርሰናል።የቀድሞ ትውልድና መሪዎች አሁን የምንኖርባትን አገር አስረክበውን አልፈዋል።

እርግጥ ሕዝብን ያስተዳድሩበት የነበረው ዘዴና ስርዓት ሕዝባዊ ጸባይና ባህሪ ባይኖረውም ጠንካራ አገር አቀፍ አቋም የነበራቸው መሪዎች እንደነበሩን አይካድም።

አሁን የእኛ ትውልድ የሚኖርበት ዘመን ጉልበተኛ የሚገዛበት፣የሰው ልጅ መብት የሚረገጥበት አይደለም።የሌላው አገር ሕዝብ መብቱን አስከብሮ እንደሚኖረው ሁሉ እኛም መብታችን ተከብሮ መኖርን እንሻለን።የሌላው አገር ህዝብ መሪዎቹን መርጦ ለሥልጣን እንደሚያበቃቸው ሁሉ እኛም የምንፈልገውን ሥርዓት ሊያሰፍኑ የሚችሉትን መሪዎቻችንን መርጠን ለሥልጣን ማብቃትን እንፈልጋለን።ሌላው አገር ሕዝብ በአገሩ ጉዳይ ላይ ባለቤት እንደሆነ ሁሉ እኛም በአገራችን ጉዳይ ላይ ባለቤት መሆንን እንሻለን።

የሌላው አገር ሕዝብ የዲሞክራቲክ መብቱ ተጠብቆ ሃሳቡን በነጻ የመግለጹን ያህል እኛም በአገራችንና በኑሯችን ላይ የሚሰማንንና የምንፈልገውን በነጻ ለመግለጽ እንወዳለን።

በመንግሥት ደረጃ የሚዘረጋ ስርዓትና አስተዳደር የግድ የሕዝቡን ተሳትፎ፣ ተቀባይነት ፈቃድ የማግኘት ግዴታ አለበትና ወደፊት ሥልጣኑን የሚረከቡ መሪዎች የእኛን የአገሪቱን ሕዝቦች የውሳኔ መብት ማክበር አለባቸው ብለን እናምናለን።።

የቀድሞውን ሳይሆን አሁን ያለው ትውልድ በሚገባ የሚያውቀውን ከአርባ ዓመት ወዲህ ያለውን ታሪካችንን ብናየው በመፈራረቅ ስልጣኑን በሃይል የያዙ ቡድኖች መብታችንን ገፈው ያሻቸውን አድርገውና በማድረግም አሁን ካለንበት ቀውስ ውስጥ ከተውን እንገኛለን።

ከዱሮ ጊዜ መሪዎች የሥልጣን አያያዛቸው በብዙም የተለየ ባይሆንም ለየት የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር የሚጠቀሙበት ቋንቋ ነው። ያለፉትን ሁለት ሥርዓቶች ልዩነትና ምስስል ብንመለከት እንደሚከተለው ሆኖ እናገኘዋለን።

1ኛ. ሕዝብ ሳይፈቅዳቸውና ሳይመርጣቸው፣የሕዝብ ቋንቋ እየተናገሩ አገር ወዳድ መስለው በመቅረብ ደርግ በሚል ስም ስልጣን ይዘው ዓይን ባወጣ ጭካኔና ሽብር በሃይል የሥልጣን ባለቤት የሆኑ ወታደራዊ አምባ ገነኖች ያሰፈኑት ስርዓት

2ኛ. በውጭ አገር ድጋፍና ፍላጎት በተጭበረበረ መንገድ ሥልጣን ይዘው፣ከአገራቸውና ከሕዝባቸው ጥቅም ይልቅ ሥልጣን ላይ እንዲወጡ የረዷቸውን የውጭ አገር መንግሥታትና ድርጅቶች ጥቅም የሚያስጠብቁ አሻንጉሊት የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ተወካይ የሆነው፣ሕዝቡን በዘርና በክልል ከፋፍሎ የሚያተራምሰው እስከ አሁን ድረስ በወያኔ የሚመራው የዘርና የክልል ሰልፈኛ የኢሕአዴግ ቡድን የዘረጋው ስርዓት።

እነዚህ  ሁለት ስርዓቶች አቀራረባቸው፣ አመጣጣቸውና ስልጣን አያያዛቸው የተለያየ ቢመስልም በጸባይና በተግባር አንድ ናቸው።

ሁለቱም ጸረ ዲሞክራሲ  ናቸው፣የሕዝብን የበላይነት አይቀበሉም

ከአገር በላይ ሥልጣናቸውን የሚወዱ፣" እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" ያለችውን አህያ አይነት አስተሳሰብ የሚከተሉ ናቸው።

እነሱ በሥልጣን ላይ የማይቆዩበት አገር ቢወረር፣ ቢበታተን፣ ሕዝብ እርስ በራሱ ቢተላለቅ፣ ደንታቸው አይደለም።

የቆሙለት ዓላማ በግልና በቡድን ጥቅም ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ ዘረፋና ሃብት መሰብሰብ ዋና ተግባራቸው ነው።

በጉልበት የያዙትን ስልጣን እንዳይነጠቁ ሌት ተቀን ተንኮል ይሸርባሉ፤የአመጽ ክንዳቸውን በሕዝብ ላይ ያሳርፋሉ፤ሲያሻቸው በውሸት ሲያሻቸው በጉልበት ዕድሜአቸውን ለማራዘም ይሞክራሉ።

ውሸትና የስለላ ሰንሰለት የስርዓታቸው ስልትና መገልገያ መሳሪያቸው ነው።

እነሱን የሚቃወመውን ሁሉ የአገርና የሕዝብ ጠላት አድርገው ያያሉ፣ይሰብካሉ፣ይገላሉ፣ያስራሉ፣ያሳድዳሉ።

የማይታመኑ ስለሆነ እነሱም ሕዝብን አያምኑም፤

ሕዝቡ የሚሠሩትንና ውስጣቸውን እንዲያውቅ አይፈልጉም፣ ከሕዝብ ጋር ሆድና ጀርባ ናቸው፤በጭፍን የሚሉትን እንዲቀበልና እንዲከተል ከማስገደድ በስተቀር ግልጽነት አይታይባቸውም።ሥራቸው ፣አካሄዳቸው ሁሉ ከሕዝብ የተሰወረና የተደበቀ ነው።

በዕድሜአችን ስልጣኑን በጉልበት እየተቀባበሉ ከዚህ በላይ የተገለጹትን ባህሪያት የተጋሩትን ስርዓቶች አይተናል አሁንም እያየን ነው።ከአሁን በኋላስ የሚቀጥለው ምን አይነት መንግሥትና ስርዓት ይሆን?በሕዝቡ  ፍላጎት አደራውን ተቀብሎ ሰርቶ የሚያሰራ መንግስት ወይስ በተጭበረበረ መንገድ ስልጣን ይዞ ነባሩ የአምባገነኖች ስርዓት እንዲቀጥል የሚያደርግ የጭበርባሪዎች የስልጣን ልውውጥ?

እርግጥ ነው ባለፉት ጊዜያቶች ለአምባገነኖችና ለዘረኞች ስርዓት መስፈን የረዳቸው ሁኔታው ነበር።ያም ሁኔታ የሕዝቡ ንቃተ ህሊና አለማደግ፣ አለመደራጀትና ሃቀኛ መሪዎች ለማፍራት አለመብቃቱ ነበር።በየጊዜው ቢታገልም፣መስዋእት ቢከፍልም ለሚፈልገው ድል አላበቃውም።አሁንስ ከዚያ ድክመት ተላቆ ለወደፊቱ የተሻለ ለማምጣት ተዘጋጅቶና ሁኔታዎችን አመቻችቶ ይገኛል ወይ?ሕዝቡ ያለውን ሥርዓት ምንነት ቢያውቅም በተዘረጋው የስለላ ሰንሰለት ምክንያት ፈርቶ ለማደር ተገዷል። አንዱን አንዱ ለማመን በመቸገሩ ይፋ ተቃውሞ ለማሰማት አልደፈረም።ደፍረው የሚወጡትን ለመደገፍና ለመቀላቀል እያመነታ ነው።በዚህም ብዙ ደፋር ታጋዮች የእሳት እራት ሆነዋል። እርግጥ ነው የህዝቡን ጥያቄና ፍላጎት የሚያንጸባርቁ ብዙ የፖለቲካ ድርጅቶችና ለሰባአዊ ሙብት መከበር የሚጮሁ ተቋማት በብዛት ተፈጥረዋል።ግን መፈጠራቸው ብቻውን በቂ አይደለም።

በተለይ በአገር ውስጥ የሚገኙት ድርጅቶች ለመንቀሳቀስ ነጻነቱ የላቸውም።ነጻነትን በትግል እንጂ በልመናና በፈቃድ እንደማያገኙት እያወቁ ከማውራት አልፈው ውጤት ያለው ሥራ ሲያካሂዱ አይታዩም።አንዳንዶቹም ድምጻቸውን አጥፍተው አንገታቸውን ሰብረው ይገኛሉ።

ተበታትነው በመገኘታቸው ተባብረው አንድ ህዝባዊ ሃይል ለመፍጠር አልቻሉም።ይባስ ብለው አንዳንዶቹ እርስ በራሳቸው የሚሻኮቱና የሚናቆሩ ናቸው። ስለሆነም ጠንካራ ተቃዋሚ ኀይል መፍጠር ተስኗቸው በእጅ አዙር በስልጣን ላይ የሚገኘውን የጋራ ጠላታቸውን እየረዱት ይገኛሉ።

ሌሎቹም በስልጣን ላይ የተቀመጠውና እንታገለዋለን የሚሉት ስብስብ  በተመሰረተበት አንጻር በዘርና በክልል ዙሪያ ያማከሉና የተዋቀሩ በመሆናቸው ለለውጥ ተነስተናል ቢሉም የሚያመጡት ለውጥ መሰረታዊና ህዝባዊ ሳይሆን፣ከክልልና ጎሳ በላይ አርቆ የማያይና አልፎ የማይሄድ በመሆኑ ህዝብን ለእርስ በርስ ግጭት የሚጋብዝ በመሆኑ ተቀባይነት የላቸውም።እንደውም በፍርሃትና በጥላቻ እንዲታዩ አድርጓቸዋል።

አንዳንዶቹም ለለውጥ ቆመናል የሚሉት ፍላጎታቸው በዚህም በዚያም ብሎ ሥልጣን ለመያዝ በመሆኑ የዓላማ ጥራትና ጥናት አይታይባቸውም።እነዚህ የሚያመጡት ለውጥ የጉልቻ ለውጥ ከመሆን አያልፍም ብሎ ሕዝቡ አንቅሮ ተፍቷቸዋል።

አንድ አገር በተለይም እንደ ኢትዮጵያ አይነቱ አገር የብዙ ሕዝብ፣የብዙ ጎሳና ነገድ፣የብዙ ቋንቋ፣የብዙ ባህል፣የብዙ እምነት፣የብዙ ሙያና ችሎታ፣የተለያዩ መደቦች፣የተለያዩ የእድሜ ጣራና የቆዳ ቀለም ያላቸው ሕዝቦች የሚኖሩበት ነው።ስለሆነም በመንግሥትነት የመሪነቱን ቦታ የሚቀበሉት ግለሰቦች ወይም የፖለቲካ ድርጅት/ድርጅቶች/ሁሉም ዜጋ ሰላማዊ ኑሮ፣እድገትን፣አንድነትን፣ፍትህና እኩልነትን የሚሻ በመሆኑ ይህንን የጋራ የህዝብ ፍላጎት በተግባር የሚተረጉም የሁሉም ለሁሉም በሁሉም የሆነ ሥርዓትና መንግሥት ማቋቋም እንጂ በህብረተሰቡ አሰላለፍ አንጻር ተደራጅቶ የአንዱን አጉልቶና የሌላውን አኩስሶ ለሥልጣን የሚታገል ግለሰብም ሆነ ቡድን ከድጡ ወደማጡ ከመሆን ያለፈ ለውጥ አያመጣም።

አንድን አገርና ሕዝብ ለመምራት በሕዝቡ ፍላጎትና ምርጫ ስልጣኑን የሚረከቡ፣የህዝቡን ደህንነት ሰላማዊ ኑሮ፣የአገርን አንድነት፣ዳርድንበር መከበር፣እውን የሚያደርጉ፤ደከመን ሰለቸን ሳይሉ በቀናነት የሚያገለግሉ ከሕዝቡ መካከል ወጥተው በሕዝቡ መካከል የሚኖሩ፣ሰርተው የሚያሰሩ የበጎ ምግባር ምሳሌ የሚሆኑ ሰዎች ስልጣኑን ሲረከቡ የሚፈጥሩት ስርዓት እውነትም የህዝብ አመኔታ የሚጣልበት መንግሥት ይሆናል።ይህንን አይነት መንግሥት ለማምጣት የሚቻለው ሕዝቡ በአንድ የትግል ጎራ መሰለፍ ሲችል ነው።ሕዝባዊ መንግሥት ለማምጣት ሕዝቡ እራሱ በሚያደርገው ትግል እንጂ አላፊነቱን ለጥቂት ዜጎች አሳልፎ በመስጠት ከዳር ቆሞ ተመልካች በመሆን አይደለም።ሕዝቡ መንግሥቱን የሚመሩትን መምረጥ ብቻ ሳይሆን ሊቆጣጠራቸውም ይገባል።ሊኖር የምንፈልገው መንግሥት ይህን አይነቱን ከሆነ ሁላችንም የምንችለውን በማበርከት በትግሉ ውስጥ መሳተፍ ይኖርብናል።

የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በአቋራጭ ወይም በሕዝቡ ውስጥ ሳይገቡ ሳይታወቁና የሕዝቡን አመኔታ ሳያገኙ መፈክር ብቻ እያነሱ ወይም በስልጣን ላይ ከተቀመጠው መወገድ ከሚኖርበት ቡድን ጋር ተደራድረን ለውጥ እናመጣለን ቢሉ ከንቱ ምኞት  ነው።ቢሳካላቸው እንኳን መሰረት የሌለው በጥቂት ጊዜ ውስጥ በሕዝብ የተቃውሞ ሞገድ ፍርክስክሱ የሚወጣ ይሆናል።ይህ እንዳይከሰት ለለውጥ ቆሜአለሁ የሚለው የተቃዋሚ ሃይል መሰረቱን በሕዝብ ላይ መጣል አለበት፤ በመካሄድ ላይ ካለው የሕዝብ ትግል ጋር በአካል መተሳሰር ይኖርበታል።ስለሆነም በሚከተሉት ወቅታዊ ተገባሮች ውስጥ ማተኮር ይኖርበታል።

በአሁኑ ወቅት በሃይማኖት ተቋማት አካባቢ የሚካሄደው እንቅስቃሴ ወደ አላስፈላጊ አቅጣጫ እንዳያመራ አመራር መስጠት፣የተለያዩ እምነት ተከታዮች እጅ ለእጅ ተያይዘው በእምነታቸው ማንም ጣልቃ እንዳይገባባቸው በመከላከል እንዲተባበሩ ማሳሰብ፣

የሃይማኖት መብት ጥያቄውን በማጣመም ሕዝቡን እርስ በራሱ ለማጋጨት የሚደረገውን ተንኮል ማጋለጥና ሕዝቡ ከዚህ ወጥመድ ውስጥ እንዳይገባ ማስጠንቀቅ፣

የአለመረጋጋቱ ሁኔታ ለተገንጣዮችና ለውጭ ወራሪዎች አመቺ ሁኔታ እንዳይፈጥር ነቅቶ መጠበቅ፣ሕዝቡንም ማደራጀት፣

የአገሪቱ መከላከያ ሠራዊት ከሕዝቡ ጎን እንዲቆም ጥሪ ማድረግ

ግለሰብ በላቡ ጥሮ ግሮ ያገኘውን ሃብት ማንም እንደማይነጥቀው ዋስትና መስጠትና ከትግሉ ጎራ እንዲሰለፍ ማበረታታት

በአገርቤትና በውጭ አገር የሚገኙት የፖለቲካ ድርጅቶች የሚረዳዱበትና አብረው የሚሰለፉበትን መንገድ/የጋራ ግንባር/መፍጠር

በአገር ውስጥ በየከተማው የምስጢር ቡድኖችን ማቋቋም፣የቅስቀሳ ጽሁፎችን ማሰራጨት፣

በውጭ አገር የድጋፍ ኮሚቴዎችን ማቋቋም፣ገንዘብና ማተሪያል ማሰባሰብ፣በሰላማዊ ሰልፍ ለውጭ አገር ሕዝብ ማሳወቅ፣ ለወያኔ ደጋፊ መንግሥታት ተቃውሞ ማሳየት፣

በስልጣን ላይ ካለው ከሚንገጫገጨው ወያኔ ከሚመራው መንግስት ተብዬ ቡድን ጋር ምንም አይነት፣ቀጥተኛም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ድርድር ውስጥ አለመግባት፣

ድርድር በእኩል ደረጃ በተቀመጡና በሚተያዩ መካከል የሚደረግ ንግግር ነው እንጂ በማይመጣጠኑ ፣ሥልጣን በያዙ ፣ የዜና አውታሮችን፣የጦር ሃይሉን፣ ገንዘቡን እንደልባቸው በሚቆጣጠሩና ምንም በሌላቸው መካከል የሚደረግ ውል አይደለም።የኋላ ኋላ የሃይለኛውን ፍላጎት አምኖ ከመቀበል በስተቀር የሚያመጣው ውጤት አይኖርም። ስለሆነም ከወያኔ ጋር ለመደራደር  በመጀመሪያ ሥልጣኑን ከሁሉም ተውጣጥቶ ለሚመሠረት ለጊዜያዊ አስተዳደር በማስረከብ ከሌሎቹ ጋር በእኩል ደረጃ መገኘት አለበት።ይህም አስተዳደር እንደጊዜያዊ /የሽግግር/ መንግሥት ሊያገለግል ይችላል።

ይህ ሳይሆን በነጮች ግፊትና ምርጫ ለውይይት መቅረብ የሕዝብንና የአገርን ነጻነት አሳልፎ መስጠት ነው።የዚህ አዝማሚያ ያላቸው ካሉ አቋማቸውን በይፋ ለሕዝብ መግለጽ አለባቸው።ሕዝቡን ካሳመኑት ሊከተላቸው ይችላል።የሚያምኑበትን በግልጽ ማሳወቅና መከተል መብታቸው ነው።ጥፋት የሚሆነው ከሕዝቡ በእስከጀርባ በሚስጥር ለመሞዳሞድ ሙከራ ካደረጉ ነው።

የራሳችን በራሳችን ለራሳችን የሆነ፣ያገራችንን ነጻነትና አንድነት የሚያስጠብቅ መንግሥት ባለቤት ለመሆን እንታገል!

ምስክር

21-08-2012